## ስንብት

ከእምነት አስተዳር

ትገነዝበቱ ልጥህ ተለጥልጦል
ትጠቀለልበት ቁርበትህ ርሶል
ትቀበርበቱ ጉድጓድ ተብጅቷል።
ብትዘላብደው ብትቀላምደው አታመልጥምና
ጀግንነቱን ጀግና
አውቆብሃልና
ሳንጃህ አያዋጣም ወኔ አይቀድምና
ጊዜ ሸንቆብሃል በቃህ አበቃልህ
የምትሄድበት ሂድ ጭራህን ቀልፈህ
ውሸትክን ስንቀህ ግባ መቃብርህ።

ጥይትህ ቢፈጅም ምን ብትንፈራፈር
ታይቶ አይታወቅም ብረት ወኔ ሲሰብር።
ያስፈሰስከው እንባ የደሙ ተውኔት
ያጨማለቅኸው ደንብ ያበላሸኸው ቤት
በግፍህ ታንፆል ሰውን አጠራቅሞ
በእምቢታ ታንፆ በፅናት ታድሞ።
ያስራብክ ያስጠማኸው ያስመረርከው ፍጡር
ያሰደድከው ድሃ ከአህጉር አህጉር
ወፈ ሰማይ ሆኖ አይኑን አጉረጥርጦ
እጆቹን ጨብጦ፣ ደረቱን ገልብጦ
ሲገሰገስ ታይቶል ልጥህን ለጥልጦ።
ጉድጓድህን ምሶ ዝግጅት ጨርሶል
ጎብዝ ተነጋግሮል እልል ተባብሎ
ማላ ተማምሎል።

“እልባሌው” ሕፃን ትናንት የገደልከው
በግፍ አደባባይ በጥይት ያስጣልከው
ሬሳውን ስትሸጥ በአይኑ እንባ አፍልቶ
ቁስሉን እያሳየ ጥሩንባውን ነፍቶ
ሸርቦል ሸርኮል ልጥህን ለጥልጦ
ደሙን አሸርጦ
ምስህን ሊግትህ መርዝህን መርዞ
አፈርክን ጎዝጉዞ
ከጥመትህና ከራስህ ትላቀቅ
ጉድጓድ አበጅቷል ካፈር ትደባለቅ።

ያስፈሰስከው እንባ አፈሯን ሰርስሮ
መሬቷም በቅቷታል አገር ምጦ ሰምሮ።
በናላህ የፈላው የጥላቻ ቡኮ

አህዛብ አስነስቶል ፍቅርን አንተክትኮ።

የሰላም ርዕዩት ጉልበቱን አንግቦ፣
ስነልቦናውን ባህሉን ስብስቦ፣
ዝምታው አልቶበት እልኩን ጨርሶ ብሶቱ ገንፍሎ፣
ብሽቀት አንጠልጥሎ፣
ብስጭቱን አዝሎ፣
በምሬቱ ግሎ፣
በአገሩ ሸልሎ፣
እንደህዝብ ጠቅልሎ፣
ለነፃነት ምሎ፣
መጣ አስገመገመ አይኖቹን አፍጥጦ ከግፏአን አምባ
ልጥህን ለጥልጠ በቆፈርከው ጉድጓድ አንተኑ ሊያስገባ።

እንደባለግክበት አገሩ አልፈረሰ
ወግድ ጉድ ወያኔ ስንብት ይድረስህ መሸኚያህ ደረሰ
ያዳፈንከው ቁጣ እሳቱ ነደደ
ያስፈሰስከው እንባ ጎርፍ ሆኖ ጋለበ
ዝም ያሉት ተነሱ የተኙትም ነቁ
ለእምቢታ ታጠቁ
ታውጀል መቃብር አንድ ሐሙስ ነው እድሜህ
ወግድ ጉድ ወያኔ ስንብት ይድረስህ።

Este_dar@yahoo.com